የሰ/መ/ቁ. 80079

ህዳር 19 ቀን 2005 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የመቶ አለቃ ጥላሁን ታችበሌ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካች ከሥራ በጡረታ ምክንያት በአሰሪ መሰናበታቸው እና ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሕብረት ስምምነት ነው ወይስ የጡረታ አዋጅ ነው የሚለው የሕግን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለመመርመር ነው፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ያቀረቡት ክስ በተጠሪ ድርጅት በጥበቃ ሰራተኝነት ተቀጥረው እስከ ታህሣሥ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውና ተጠሪ ድርጅት ጡረታን ምክንያት አድርጎ መብታቸውን ሳይጠብቅ ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠ በመሆኑና ስንብቱ ሕገወጥ በመሆኑ ሕጉ በሚፈቅደው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው ጠይቋል፡፡ ተጠሪ ድርጅት በሰጠው መልስ በድርጅቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ተጠሪ የሠራተኞችን የጡረታ መውጫ ጊዜ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ አመልካችም ዕድሜያቸው 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የፕሮቨደንት ፈንዳቸው ተከፍሏቸው በልዩ ሁኔታም የሁለት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ተሰናብቷል፡፡ ስንብቱም በአግባቡ የተከናወነ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር ያደመጠው የሥር ፍርድ ቤት ስንብቱ በሥራ ላይ ባለው የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊ ነው፡፡ ምንም ክፍያ መጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት የይግባኝ ባይ ቅሬታን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አፅንቷል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤቱ ፈጽሞታል ያሉትን የሕግ ስህተት በመዘርዘር ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ በአመልካች አቤቱታ ከተዘረዘሩት የቅሬታ ነጥቦች የጡረታ ዕድሜ በሕግ እንዲ

በሕብረት ስምምነት ሊወሰን እንደማይገባ፤ አሰሪው /ተጠሪ/ ተቋም ሕገወጥ ስንብት የፈፀመ በመሆኑ የ6 ወር ደመወዝ በካሣ መልክ እንዲከፍላቸው እንዲወሰንላቸው አመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ 1ኛ የሥራ ክርክር ችሎት በተመሣሣይ ጉዳይ በመ/ቁ 62433 ህዳር 11 ቀን 2004 ችሎት የጡረታ ዕድሜ አግባብ ባለው ሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት የሚወሰን አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዲታይላቸው አያይዘው አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት በተጠሪና በሠራተኞች ማህበር መካከል በተፈረመው የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 32.5 መሠረት ነው፤ ተዋዋይ ወገኖችም የጡረታ ዕድሜን ሊወስኑ እንደሚችሉ የሕብረት ስምምነቱን የፈረሙት ተዋዋይ ወገኖች የተስማሙ በመሆኑና አመልካች በዚህ አግባብ በሕጋዊ መንገድ የተሰናበተ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት አመልክቷል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ ቅሬታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚገዙ ሠራተኞች የጡረታ ዕድሜ የሚወሰነው አግባብ ባለው ሕግ ነው ወይስ በሕብረት ስምምነት? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር በጥበቃ ሠራተኛነት ሲሰሩ እንደነበረ፤ በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 32.5 መሠረት 55 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ ተጠሪ መወሰኑ ከሥር ፍርድ ቤቶች መዝገብ መገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች የጡረታ ጉዳይ መታየት ያለበት በሕግ እንጂ በሕብረት ስምምነት አለመሆኑን አጥብቀው ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ የሕብረት ስምምነቱ በተጠሪ ድርጅት እና በሠራተኛ ማኀበር የተፈረመና ተግባራዊ መሆኑ ከሕግ እንደማይቃረን አመልክቷል፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የነበረው የሥራ ውል ግንኙነት ከሚቋረጥባቸው መንገዶች አንዱ ሠራተኛው በጡረታ ሲገለል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ጭብጥ የጡረታ መውጫ ጣሪያ ዕድሜ ስንት ነው? በሕግ ነው የሚወሰን ወይስ በሕብረት ስምምነት የሚለው ነው፡፡ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ በግልጽ አልደነገገም፡፡ ይሁንና አዋጁ በአንቀጽ 24/3/ “ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በጡረታ ሲገለል” የሥራ ግንኙነቱ በሕግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ ማህበር የሚፈረመው የሕብረት ስምምነት በተመሣሣይ ጉዳይ ለሠራተኛው በሕግ ከተደነገገው ይልቅ የሕብረት ስምምነቱ የበለጠ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው በአንቀጽ 134/2/ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ያለፈቃዳቸው በጡረታ ከሥራ እንዲሰናበቱ የተደረገ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ተጠሪም የስንብት ድርጊቱ የተፈፀመው ለሠራተኛው የተሻለ ጥቅም የሚሰጥ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በስንብት ስርዓቱ የሕብረት ስምምነት የተፈፀመ ነው ይበል እንጂ የሕብረት ስምምነቱ አግባብነት ካለው ሕግ በተሻለ መንገድ ለሠራተኛው የጠቀመ ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ክርክር አልተረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የሕብረት ስምምነቱ የጡረታ ዕድሜን ከመወሰን አኳያ የተፈፃሚነት ወሰን ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህም በቀር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሁለት የተለያዩ ምድብ ችሎቶች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24/3/ አተረጓጐም ላይ የተለያየ አቋም ወስደዋል፡፡ ይህ ደግሞ አዋጁን ወጥ በሆነ አግባብ ከመተርጎም አንፃር የራሱ የሆነ ውስንነት እንዳለው እንዲሁም የተከራካሪ ወገኖችን በሕግ ፊት እኩል የመዳኘት መብት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡ አንደኛው ምድብ ችሎት በሕብረት ስምምነት የተወሰነውን የጡረታ ዕድሜ ጣሪያ ሲቀበል ሌላኛው ምድብ ችሎት አግባብነት ያለው ሕግ ማለት የሕብረት ስምምነት አለመሆኑን በመጥቀስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

አከራካሪው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሕግ የምንለው የትኛው ነው የሚለው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሕብረት ስምምነቱ በአንቀጽ 24/3/ የተመለከተውን ትርጓሜ የማይካተት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ የምንለው ሥልጣን ባለው አካል የወጣ ሕግ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በአስፈጻሚው አካል የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የሚያካትት መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የጡረታ ዕድሜ መውጫን በተመለከተ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተለያየ የዕድሜ ጣሪያ የተቀመጠ ቢሆንም በሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንዲሁም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17/1/ የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት መሆኑን ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለው ሕግ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች አዋጅ እንደ አግባብነቱ ወይም የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ሆኖ ሳለ የሕብረት ስምምነቱን መውሰዳቸው መሠረታዊ የሕግ አተረጓጐም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት በኮ.መ.ቁ 63787 በ27/02/2004 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 115690 በ02/8/2004 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. ግሎባል ሆቴል ኃላ.የተ.የግል ማህበር እና የተቋሙ ሠራተኞች ማህበር የፈረሙት የሕብረት ስምምነት የጡረታ መውጫ ዕድሜን በተመለከተ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም ብለናል፡፡
3. ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር በተነሱት የክፍያና ተያያዥነት ያላቸው የመብት ጥያቄዎችን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ